NEIGHBOURHOOD

Empowerment Team

# ወንጀል መከላከል

## ኣከባቢን ባገናዘበ ዕቅድ

የኢድመንተን ነዋሪዎች ንብረትዎ ለመጠበቅ ፈጣንና ተግባራዊ የሆነ መምርያ ይጠቀሙ።



# ኣከባቢ ያገናዘበ ስልት በመጠቀም ወንጀልን መከላከል (CPTED)



የንብረት ስርቆት ለምሳሌ፥-**ከመኪና** ወይም **ከቤትዎ ኣከባቢ ዕቃ መሰረቅ** ለወንጀል በር ከፋች ነው።

**CPTED የኣከባቢ ኣቀማመጥ በመቀየር ሊፈጠሩ የሚችሉ ወንጀሎችና የወንጀል ፍራቻ ለመቀነስ በተግባር የተረጋገጠ ስልት ነው። የ CPTED ስልቶች በተነሳሽነት በመተግበር የንብረታችንና የሕ/ሰባችን ደህንነት ማሻሻል ይቻላል።**

የቦታ ኣቀማመጥ ኣስተዳደር የሰዎች ባህርይ ላይ ተጽዕኖ ያመጣል። ቦታ ኣቀማመጥ በትክክል ከሆነ ወንጀል በመቀነስ የደህንነት ግንዛቤ ይጨምራል። ነገርግን የቦታ ኣቀማመጥ ጥሩ ካልሆነ ወንጀልና ጸረ-ሕ/ሰብ ባህርይ እንዲፈጠር ያደርጋል። ይህም ደግሞ ደህንነታችንና የሕ/ሰብ ተሳትፎ ፈቃደኝነት ተጽእኖ መፍጠር ብቻ ሳይሆን ኣጠቃላይ ደህንነታችን ተጽእኖ ያመጣል።

ዒላማ ማጠናከርያ ስልቶችን ተግባራዊ በማድረግ የቤት ባለቤቶች ኣስቀድሞ ወንጀል መከላከል ይችላሉ። እነዚህ ስልቶች የ CPTED (ኣከባቢ ያገናዘበ ስልት በመጠቀም ወንጀልን መከላከል) መርሆች በመከተልና የኣከባቢ ኣቀማመጥ ስልት ለመንደፍ ወንጀል መከላከል ይቻላል። ጥሩ ስልት ሌባ የመያዝ ዕድል በመጨመር ከወንጀል የሚገኙ ጥቅሞችም ይቀንሳል።በተጨማሪ ለመኖር ምቹ ኣከባቢ ይፈጥርልናል።

**CPTED በደንብ የሚሰራው በጋራ ነው። ስለሆነም የቤት ባለቤቶች እነዚህ የተጠቀሱ ጠቃሚ ምክሮችን በመተግበር የቤትዎ ደህንነት መጨመር ይቻላል።**



# ክትትል

**የማየትና የምታየት** ስሜት።

**አከባቢያችን ቀድሞ በመተንበይ ምቾት እንዲሰማን** ያደርጋል።

**የግል ምስጢር በጠበቀ ሁኔታ ቦታዎች ለማየት** ግልጽ አቀማመጥ ሊኖራቸው ይገባል።

**ተነጥሎ ወይም የተደበቁ ቦታዎች ሊኖሩ አይገባም።**



**መጥፎ**



**ጥሩ**



የመብራት ውጥረት ወደ ተፈለገው ቦታ መብራት ያስተላልፋል።

መብራት ነጸብራቅና ጥላ በመለየት ክትትል ለማድረግ ጠቃሚ መሳርያ ነው። ወጥነት መኖሩ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ለሌሊት ዕይታ ተጽእኖ ስለሚፈጥር በጣም ደማቅና በጣም ዝቅተኛ መብራት ሊኖር አይገባም።



ለወንጀል ተጋላጭ የሆነ ቦታ ካሜራዎች፥ ኣላርም፥መስታወቶችና የመብራት ዳሳሽ ማድረግ ለማየት **ያግዙናል።**

# ክትትል




## በቀላሉ ክትትል ማድረግ

**ሰዎች ኣከባቢያቸውን በመንቀሳቀስ ክትትል** ማድረግ ይችላሉ።

በቤትዎ ኣከባቢ የሚያልፉ ሰዎች **የሚጠራጠሩትን እንቅስቃሴ መከታተልና ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።**

የግንባታ ዕቃዎች ፥ የመሬት ኣቀማመጥ፥ ኣጥርና ግድግዳ በቀላሉ ክትትል ሊደረግበት በሚችል ሁኔታ ሊሰሩ ይችላሉ። የመሬት ኣቀማመጥ ቀላሉ ደንብ **ቁጥቋጦ በ0.6 ሜትር (2 ፊት) መከርከምና የዛፍ ቅርንጫፎችን ወደ 1.8 ሜትር (6 ፊት)** የኣይን ዕይታ ማሳጠር ነው።

**የጥበቃ ክትትልና ኣከባቢ ጥበቃ** መርሃግብር ጠቃሚ ምልከታዎች መስጠት ብቻ ሳይሆን የማ/ሰብ ተሳትፎ ያሳያል።

ከጋራ መሬት ኣጠቃቀም ክትትልና (የኣከባቢ ነዋሪዎች ቀን ሳይኖሩ ንግድ የሚሰሩ ሰዎች) ከቅርብ የሚገኙ ኣገልግሎት የሚሰጡ **ማጫወቻዎች ማህበረሰቡ ይጠቀማል።**

## ሌሎች ክትትሎች



**የተፈጥሮ ማስተላለፍያ ክትትል**
የመሬት ኣቀማመጥና የህንጻ ዲዛይን የሚያጠቃልለው፥ የእግረኛ፥ የኣትክልትና የተለያዩ የመሬት ገጽታዎች ናቸው።

# የተፈጥሮ ማስተላለፍያ ክትትል



ቤት **የሚገቡ ወይም የሚወጡ** ሰዎች ይቆጣጠራል።



**የማምለጫ መንገዶችን መዝጋት።** ለኣደጋ የተጋለጡ ቦታዎች በመከላከል ሰዎች በየት መሄድ እንዳለባቸው ማሳየት ነው።



**በትክክል የመንገድ ኣቅጣጫ ካስቀመጥን** ትክክለኛ ሰዎች የሆኑና ያልሆኑ መለየት ቀላል ነው።





### ሌሎች መተላለፍያ መቆጣጠር

ኣጥርና በር በማድረግ ያልተፈለገ ሰው እንዳያልፍ መከልከል ይቻላል።

እነዚህ የተወሰኑ ቦታዎች በመከልከል ክፍት የሆነ ዕይታ መከልከል ይቻላል።

ካርድ ኣንባቢ ወይም የመቆለፍያ ዘዴ በር ላይ በማድረግ በመግብያ በኩል የተፈቀደለት ሰው ብቻ እንዲገባ ያግዛል።



# የግዛት ክልል



በደንብ የተከለለ ቤት ቦታው **ክትትልና እንክብካቤ** መኖሩ ያሳያል። ስለሆነም ወንጀለኛ ገበን  የመፈጸሙ ዕድል ትንሽ ነው።

## መከላከያ ቦታ

የቤቱ ቦታ **ወሰን** በትክክል ይታይ።

ከህዝብ መንገድ ወደ ግል ቤት መተላለፍያ መንገድ መኖር ኣለበት።



በፊት



በኋላ

## ጥገና

**በደንብ የተጠገነ** ቤት ኲራትና የባለቤትነት መንፈስ በማሳየት ላልተፈለገ ነገር ትዕግስት እንደሌለው ያሳያል።

በደንብ ያልተያዙ ቤቶች በባለቤቱ በደንብ እንክብካቤ ኣለመኖሩ ያሳያል። ስለሆነም ለወንጀል የመጋለጡ ዕድል ሰፊ ነው።






# በቤታችሁ አከባቢ CPTED በመጠቀም




በቤታችሁ አከባቢ ........ ገጽ 7


መስኮቶች ........ ገጽ 8


በሮች ........ ገጽ 9


ጋራዥ ........ ገጽ 10


ዕቃ ክፍል ........ ገጽ 11



**ውድ ዕቃዎች በትክክል ማስቀመጥ**
ከዕይታ ውጭ ማድረግ።

# በቤትዎ አከባቢ

ወደ ቤትዎ የሚወስደው መንገድ በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት። ማለትም **አትክልቶቹ መከርከምና ደማቅ መብራት** መኖር አለበት። ስለሆነም የአከባቢ ሰዎች ተጠርጣሪ ሰው ለማየት ስለሚያግዛቸው የሚፈጠረው አደጋ ይቀንሳል።



ቤትዎ ከህዝብ ንብረት ለመለየት **የመሬት አቀማመጥ** በመጠቀም ጎብኚዎች ወደ ተፈለገው  መግብያ እንዲያመሩ ይደረጋል።

ቤትዎ በትክክል ጥገና የተደረገለትና የተስተካከለ ቁመና ይኑሮው። ይህ ማለት ለቤትዎ ጥሩ እንክብካቤ እንደሚያደርጉ ያሳያል።






የቤትዎ **አድራሻ በትክክል የተጻፈና መብራት ያለበት መሆን** አለበት። ይህ መኪኖች በአደጋ ጊዜ በቀላሉ አድራሻው ማየት ይችላሉ። በቤትዎ ጀርባም አድራሻ እንዲኖሮው አድርግ።



በቤት ውስጥ ከሌሉ መስኮት ክፍት አይተዉት። **ሌባ የ2ኛ ፎቅ መስኮት መጠቀም ይችላል።**

# መስኮቶች



መስኮቶቹ መዝግያ ካላቸው ተጠቀሙ። ከሌላቸው **መስኮቶቹ እንዳይከፈቱ ተጠንቀቁ ወይ የበር መዝግያ ኣድርጉላቸው።**

**የደህንነት ብረት ማድረግ** ነገርግን በኣደጋ ጊዜ **በቀላሉ የሚከፈት መሆን ኣለበት።** የምድርቤት መስኮቶች በሌቦች የመሰበር ዕድል ሰፊ ነው።




**የማይሰበር ላሚኔት** ወይም **ብረት ማሳያ ሽፋን** በማድረግ የመስኮቱ ደህንነት መጠበቅ ይቻላል።




የሚሰበር



የብረት ማሳያ ሽፋን



ላሚኔት




እቤት ከሌለህ **ውድ ዕቃዎችን ከዕይታ ለመደበቅ መጋረጃዎችን ዝጋ** ነገር ግን እቤት ከሆንክ ሰው መኖሩን ለማሳየት ክፈተው።



የውጭ በሮች **ጠንካራ ብረት** መኖራቸው ኣረጋግጥ።

# በሮች

በበር ኣጠገብ **የብረት መዝግያ** ግጠምለት።



ዘልቆ የሚገባ መቆለፍያ ቢያንስ **1 ኢንች** ሊሆን ይገባል። ይህ ከበሩ ወደ ፍሬም **ዘልቆ** የሚገባ መሆን ኣለበት።





የበሩ ማጠፍያዎችና በሰሌዳ ውስጥ ያሉ ብሎኖች ቢያንስ **3 ኢንች** መሆን ኣለባቸው።




ወደ ቤትህ ከመግባትህ በፊት የጋራዡ መስኮት **ሙሉ በሙሉ መዘጋቱ** አረጋግጥ።

# ጋራዥ



የቤትህ ጋራዥ ከቤት የተያያዘ ከሆነ ከጋራዡ መግብያ በር **ጠንካራና መቆለፍያ ያለው** መሆኑ አረጋግጥ። ካልሆነ ሌባ ጋራዡ ሰብሮ ከገባ በኋላ ወደ ቤትህ ይገባል።

ውድ ዕቃዎችን ከስርቆት ለመጠበቅ **የመስኮት መጋረጃ** ተጠቀም።





አውቶማቲክ የጋርዥ መክፈቻ **መኪና ውስጥ አታስቀምጥ።** ሌባ መኪናህን ሰብሮ ጋራዥ መክፈት ይችላል።

ጋራዡ ከቤት የተያያዘ ካልሆነ ትክክለኛ **መብራት በአከባቢው** መኖሩ አረጋግጥ።

የጋራዥ መግቢያ በሮች **እንደቤቱ መቆለፍያና ተመሳሳይ ዘዴ** መጠቀም አለበት።

**ከቤት ርቀህ ስትሄድ የአውቶማቲክ መክፈቻ እንደማይሰራ አድርገው።** የጋራዡ የላይኛው በር ወደ ኋላ ስለሚነሳ ከውጬ መግባት ይቻላል። የጋራዥ በሮች ማጠናከርያ ከኦንላይን ብዙ ዘዴዎችን ማግኘት ይቻላል።







በዕቃ መጋዘን ያለው ዕቃ **በጣም ውድ** ሊሆን ይችላል።

# መጋዘን



የውጭ በር መቆለፍያ፡ **እንደ ዕቃ ማስቀመጥያ በደንብ ይጠቅማል።**

የዕቃ መጋዘን ጠንካራና **በቀላሉ የማይቆረጥ** መሆን አለበት።

በመጋዘን ያሉ ውድ ዕቃዎች **ላለማሳየት** መስኮቶች መሸፈን አለባቸው።



መጋዘን አከባቢ ያለው **መብራት በደንብ የሚያበራና በሩ ጠንካራ መሆን አለባቸው።**





ሁሉም **ዕቃዎችና የመቆለፍያ ቁጥሮች መመዝገብ** አለባቸው።

NEIGHBOURHOOD
Empowerment Team

የኢድመንተን ፖሊስ ወንጀል መከላከል ክፍል ለሁለቱም ህግ ኣስከባሪዎችና ለኣባላት CPTED ስልጠና ይሰጣል።

**edmontonpolice.ca | 780-421-3422**

በዚህ ጽሁፍ የበለጠ መረጃ ማግኘት ከፈልጉ **NET@edmonton.ca** ያነጋግሩ።

NET ማለት ከኢድመንተን ፖሊስ ፥ ከኢድመንተ ከተማ፥ ከፋሚሊ ሰንተርና ዩናይትድ ወይ ኦፍ ዘ ኣልበርታ ካፒታል ርጂን ተባብሮ የሚሰራ ነው።

የታተመው፥ በጋ 2019 | Amharic